# ከሕዝብ ልብ የራቀ፣ ከህዝብ ድጋፍና ድምፅም ይርቃል

## ክፍል ሁለት

ለሚ ዋቁ  09-24-14

በዚሁ ርዕስ በቀረበው ክፍል አንድ ፅሁፍ ላይ አንድነት፣ መኢአድና ሰማያዊ ፓርቲ የተመሰረቱበትን ዓላማና በህገመንግስቱ ላይ ያላቸውን የተቃውሞ አቋም አንስተናል። ፓረቲዎቹ ይህን በህገመንግስቱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በፓርቲ ፕሮግራምና በድርጊትም ሲቃወሙ መቆየታቸውን እና ተያያዥ ጉዳዮችን ደግሞ በዚህ ፅሁፍ ላይ እንመለከታለን።

አንደነት፣ መኢአድና ሰማያዊ ፓርቲዎች በይፋ ከያዙት የኢትዮጵያን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብትና ነፃነትን ከሚፃረረው አቋማቸው ልጀምር። እነዚህ ፓርቲዎች በዚህ ጉዳይ ላይ የያዙት አቋም በሕገመንግሥቱ ላይ ከሰፈረው ይፃረራል። የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት አንቀፅ 39 "የብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች መብት" በሚል ርዕሥ ሥር የሚከተለውን ደንግጓል፤

- *ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማንኛውመ መልኩ የተጠበቀ ነው።*
- *ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባህሉን የመግለፅ የማዳብርና የማስፋፋት እነዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው።*
- *ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት በሄሩ፣ ብሄረሰቡ፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልከዓምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግስታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በውክልና በፌደራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል።*

እንግዲህ አንድነት፣ መኢአድና ሰማያዊ በፓርቲዎቻቸው ፕሮግራም ላይ፤ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች በሕገምንግሥት የተረጋገጠላቸውን እስከመገንጠል የሚደስ የራስን

እድል በራስ የመወሰን መብት “ሃገሪቱን ለመበታተን አደጋ ያጋልጣል” በሚል ይቃወሙታል።

በቅድሚያ የብሄሮች፣ ብሄረቦችና ሕዝቦች እስከመገነጠል የዘለቀ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት በሌላ አካል የተሰጣቸው ሳይሆን ራሳቸው የወሰኑት ነው። የሃገሪቱ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች በሆኑትና በመከባበርና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲኖራቸው በተስማሙት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የተወሰነ ነው። ይህን እሰከመገነጠለ የዘለቀ መብት በህገመንግስቱ ላይ ያሰፈሩት ለመበታተን ሳይሆን መብትና ነፃነታቸው ተረጋግጦ በእኩልነት መኖር ለመቻላቸው ዋስትና እንዲሆናቸው ብቻ ነው። ብሄራዊ መብቶቻቸውና ነፃነቶቻቸው ሕገመንግሥቱ ላይ በሰፈረው መሰረት ካልተረጋገጠላቸው፣ የመገንጠል ጥያቄው የብሄሩ ወይም የብሄረሰቡ መሆኑን በሚያረጋግጥና በዛው መብቱን በሰጠው ሕገመንግሥት ላይ በተደነገገው ሥረአት መሰረት በሕዝበ ውሳኔ ነፃ መንግሥት የመመስረት መብት የሚሰጥ ነው።

አንድን ብሄር ወይም ብሄረሰብ እንዲገነጠል ወይም ከሌሎች ጋር አብሮ እንዲኖር የሚያደርገው እስከመገንጠል የዘለቀ መብት በሕገመንግሥት መደንገግ ወይም አለመደንገግ አይደለም። ብሬራዊ ጭቆና እስካለ ድረስ ህገመንግሥቱ የመገንጠል መብት ፈቀደም አልፈቀደ የመገንጠል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው። የኤርትራ ልጆች የመገንጠል ጥያቄ ያነሱት በኋላም የተገነጠሉት የመገንጠል መብት በህገመንግስት ስለተፈቀደ አልነበረም። በቅርቡ ስኮትላንድ ከዩናይትድ ኪንግ ደም የመገንጠል ጥያቄ አንስታ ህዝበ ውሳኔ የተካሄደው የዩኬ ሕገመንግስት መገንጠልን ሥለሚፈቅድ ወይም ሥለሚያነሳሳ አይደለም። በሕገመንግስት ላይ እስከመገንጠል የዘለቀ መብት መኖሩ ግን መብትና ነፃነት ለመከበሩ ዋስትና ይሰጣል። በኢፌዴሪ ሕገመንግስትም የተደረገው ይሄው ነው።

በመሆኑም አንድነት፣ መኢአድና ሰማያዊ ፓርቲ እስከመገነጠል የሚዘልቀውን የህገመንግስቱን ድንጋጌ የተቃወሙት እርግጥ የመገንጠል አደጋ ሥለሚያስከትል ሳይሆን በመርህ ደረጃ የብሄሮችን፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦችን ራስን በራስ ማስተዳደርና እኩልነት ሥለሚቃወሙ፣ በኢትዮጵያ “የአንድ ብሄር የበላይነት የሰፈነበት አሃዳዊ መንግስት መመስረት አለበት” ብለው ስለሚያምኑ ነው። ሕገመንግሥቱና ሕገመንግሥታዊ ሥርአቱ

ላይ እንዲሁም ሕገመንግሥቱን የተቀበሉ ላይ የመረረ ጥላቻና ተቃውሞ ያደረባቸውም በዚህ አቋማቸው ምክንያት ነው።

አንድነት፣ መኢአድና ሰማያዊ በሕገመንግስቱ የተደነገገውን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሥርአት አወቃቀርንም ይቃወማሉ። ፓርቲዎቹ የሃገሪቱ አሰተዳደራዊ አወቃቀር በብሄር፣ ብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን መልከዓ ምድራዊ - ወንዝ፣ ሸለቆ፣ ገደል፣ ተራራ . . . ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት ባዮች ናቸው። በመሰረቱ ሃገር ግኡዝ መሬት፤ ወንዝ፣ ሸለቆ፣ ገደል፣ ተራራ . . . አይደለም። ሃገር ማለት መብትና ነፃነት፤ ጥቅምና ፍላጎት ያለው ሰው - ሕዝብ ነው። በመሆኑም የሃገር አስተዳደራዊ አከላለል ግኡዝ መሬት ላይ እንዲሆን መጠየቅ መብትና ነፃነት፤ ጥቅምና ፍላጎት ላለው ሕዝብ ዋጋ አለመስጠት ነው።

ይህ የተቃዋሚዎቹ አቋም የወራሪ ቅኝ ገዢዎችና የተስፋፊ ፊውዳሎች አመለካከት ነው። ቅኝ ገዢ ወራሪዎችና ተስፋፊ ፊውዳሎች ከመሬት ላይ የሚገኘውን ጥቅም ብቻ ስለሚያስቡ፣ በመሬቱም ላይ የሰፈረው ሕዝብ ይህንኑ ቁሳዊ ፋይዳ የሚያስገኝላቸው መሳሪያ ብቻ አድርገው ስለሚያስቡ ሃገርን እንደ ሕዝብ አያስቡም፤ እንደ መሬት እንጂ። እነ አንድነት የዚህ አይነት አቋም የያዙት ሥለህዝብ ምንም ደንታ ሥለሌላቸው ነው። ድሮ ገድለን የቀበርነው፣ ጥቂቶች በፈጣሪ ገዢነት ተቀብተናል የሚሉ ነገስታት የአንድ ብሄርና ሃይማኖት የበላይነት ያለው አሃዳዊ የመንግስት ሥርአት መስርተው የገዙበትን ዘመን የመመለስ ምኞት ያላቸው ተስፋ ለዘውድ ናቸው።

አንድነት፣ መኢአድና ሰማያዊ ፓርቲ የያዙት ይህ የሃገር ምንነት ላይ ያለ አመለካከት ግዙፍ የመርህ ሥህተት ያለበት ከመሆኑ ባሻገር፣ ወደ ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ሥንመልሰው የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በኢፌዴሪ ሕገመንግሥት *"ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት በሄሩ፣ ብሄረሰቡ፣ ሕዘቡ በሰፈረበተ መልከዓምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋም የማቋቋም እነዲሁም በክልልና በፌደራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል።"* በሚል ድንጋጌ የተጎናፀፉትን መብት የሚፃረር ነው። በአጠቃላይ ይህ አቋም ከዘረኝነትና ይህ ዘረኝነት

ከተወለደው በሌሎች የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ላይ ካለ ንቀትና ጥላቻ የመነጨ ነው።

ከላይ ከተገለፀው የአንድነት የየመኢአደና የሰማያዊ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብት፣ ነፃነትና እኩልነት ላይ ካላቸው ፕሮግራም የተያዘ የተቃውሞ አቋም በተጨማሪም ይህንኑ የመብትና የነፃነት ተቋውሟቸውን በድርጊት የገለፁበትን ሁኔታም ታዝበናል። ይህም ከኢፌዴሪ ሰንደቅዓላማ ጋር የተያያዘ ነው። የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት በአንቀፅ 3 "የኢትዮጵያ ሰንደቅዓላማ" በሚል ርዕስ ሥር፤

- *የኢትዮጵያ ሰንደቅዓላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሃል ቢጫ፣ ከታች ቀይ ሆኖ ብሄራዊ አርማ ይኖረዋል*
- *ከሰንደቃላማው ላይ የሚቀመጠው ብሄራዊ አርማ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች እና ሃይማኖቶች በእኩልነትና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንፀባርቅ የሆናል።*

ይላል።

በዚህ የህገመንግሥቱ ድንጋጌ መሰረት የኢትዮጵያ ሰንደቅዓላማ ሦስቱ ቀለሞች ላይ ያረፈ ብሩህ ሰማያዊ ቀለም ክብ መደብ ላይ ባለአምስት ማዕዘን ቢጫ ኮከብና ጮራ የፈነጠቀበት አርማ እንዲኖረው ተደርጓል።

አንደነት፣ መኢአድና ሰማያዊ ፓርቲ ይህን የኢትዮጵያ በሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ሃይማኖቶች እኩልነትና በእኩልነት አበሮ ለመኖር ያለን ተስፋ የሚወክል ሰንደቀዓላማ አለተቀበሉም። ጽህፈት ቤቶቻቸው ውስጥ ግድግዳ ላይና በሌሎችም ሥፍራ የሚለጥፉት አርማ የሌለውን ሰንደቅዓላማ ነው። ከዚህ ቀደመ ባደረጓቸው ሰላማዊ ሰልፎች ላይ ይህን ሰንደቅዓላማ ይዘው አልወጡም። ባለፈው ዓመት አንድነትና ሰማያዊ ፓርቲ በአዲስ አበባላይ ባካሄዱት የተቃውሞ ሰልፍ ላይ አንድም ባለአርማ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አልታየም። ዓርማ የሌለውን ሰንደቅዓላማ ማውለብለብ በሕግ ስለሚያስጠይቅ የተበጣጠሱ አረንጓዴ ብጫና ቀይ ጨርቆችን ነው ያውለበለቡት።

ይህ ለሰንደቃላማው ያላቸውን ንቀት በቅልፅ ያሳያል። ለሰንደቃላማው ያላቸው ንቀት ደግሞ ለኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ካላቸው ንቀት የመነጨ ነው። በልባቸው የመስቀል ምልክት ባለው መቆሚያ ላይ የይሁድ አንበሳ ሰንደቅዓላማ የሚያውለበልብበት ዓርማ ያለበትን የዘውዳዊ ሥርአት ሰንደቃላማ ማውለብለበ እነደሚፈልጉ እነሱም ያውቃሉ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦችም ያውቃሉ።

እዚህ ላይ የተለያዩ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ፓርቲዎችን ያቀፈውና አንድነት "አብሬ መዝለቅ አልፈልግም" ብሎ ጥሎ የወጣው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ አንድነት መድረክ ወይም መድረክ አንድነትና ሰማያዊ ፓርቲ የተቃወሞ ሰልፍ በጠሩበት ሰሞን ጠርቶት የነበረው የተቃውሞ ሰልፍ በሚያሰደንቅ ሁኔታ በባለአርማው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያሸበረቀ ነበር። ይህ አንድነትና ሰማያዊ ፓርቲ በሰንደቃላማው ላይ ያላቸው ጥላቻ ለብሄር ብሄረሰቦች ካላቸው ጥላቻ የመነጨ መሆኑን በግልፅ ያረጋግጣል።

በገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ላይ ያላቸው ጥላቻም ከዚሁ የመነጨ ነው። በአጠቃላይ ፓርቲዎቹ ከመፃኢ የኢትዮጵያ ህዝብ የእኩልነትና የብልፅግና ተስፋ ሳይሆን ከጥላቻ በመነጨ ስሜት የተመሰረቱ ፓርቲዎቸ ናቸው። ጥሩውን ከመጥፎ መለየት ሳያስፈልጋቸው መንግሥት የሚሰራቸውን ሁሉንም ነገር የሚቃወሙት፤ መንግስትን የሚቃወም የሚመስላቸውን ሁሉንም ወገን የሚደግፉት ለዚህ ነው።

ፓርቲዎቹ በዚሀ ምክንያት ሕዝባዊ መሰረት አጥተዋል። ይህ ደግሞ የመንግሥት ሥልጣን ለመረከብ የሚያበቃ የህዝብ ድምፅ ማግኘት እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። ፓርቲዎቹ አሁን በያዙት አቋምና አመለካከት በኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ውክልና ወደሥልጣን መምጣት የሚችሉበት መንገድ ሙሉ በሙሉ ተከርችሟል። በምርጫ ላይ የመፎካከር ጉለበታቸው ልምሻ ሆኗል።

አንደነት፣ መኢአድና እንጭጩ ሰማያዊ ፓርቲ ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንዳነሳነው ከሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት፣ መብትና ነፃነት ሳይሆን በጥላቻ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው በውስጣቸውም የተለያየ አቋሞችንና አመለካከቶችን ማስተናገድ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። በመስራች አመራሮቹ ውስጥ ካለ ጭፍን ጥላቻና ከዚህ በመነሳት ከየትኛውም የኢፌዴሪ

ህገመንግስት ጠላት ጋር ለማበር ካለ  አመለካከት ውጭ ሌላ አመለካከት ለማስተናገድ ፍቃደኝነቱ የላቸውም። በአጠቃላይ ፓርቲዎቹ የመስራቾቹ ርስቶች ናቸው። ውስጠ ዴሞክራሲ የላቸውም።

በመሆኑም በውስጣቸው ያሉ ልዩነቶችንና የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በውይይትና በዴሞክራሲያዊ መንገድ የመፍታት ባህል ማዳበረ አልቻሉም። በዚህ ምክንያት አለመግባባት፣ ጭቅጭቅ፣ ፍርድቤት መካሰስ፣ እንደወሮበላ በጡጫና በግርጫ በዱላና በድንጋይ መደባደብ መፈናከት መለያቸው ለመሆን በቀቷል።

ከጥቂት አመታት በፊት አንድነት ፓርቲ ሕጋዊ እውቅና ያገኘበት መዝገብ ላይ የተፃፈበት ቀለም ሳይደርቅ በውስጥ አለመግባባት ተፈጥሮ እንደነበር እናስታውሳለን። በአንድ ወገን እነ ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም፣ በሌላ ወገን እነ ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው ልዩነታቸውን በውይይትና በዴሞክራሲያዊ መንገድ መፍታት አቅቷቸው እነደወሮበላ በድንጋይና በዱላ መፈነካከታቸውን፣ ጥርስ መሳበራቸውን እናስታውሳለን።

አንድነት አሁንም ከዚህ ኢ. ዴሞክራሲያዊ ባህሪው አልተላቀቀም። በቅርቡ "ከመኢአድ ጋር ውህደት እመሰርታለሁ" ብሎ መነሳቱን ተከትሎ በውስጡ በተፈጠረና መፍትሄ ሊበጅለት ባልቻለ አለመግባባት ሳቢያ አምሥት የስራ አስፈፃሚ አባላቱ ራሳቸውን ከሃላፊነት አንስተዋል።

ሌላው አለሁ ባዩ ፓርቲ መኢአድም የተመሳሳይ ችግር ቁራኛ ነው። ከሁለት ዓመት በፊት በወቅቱ የመኢአድ ሊቀመነበር በነበሩት ኢ/ር ኃይሉ ሻውልና ዶ/ር ታዴዎስ በተባሉት ሌላው አመራር መሀከል በተነሳ የሥልጣን ይገባኛል ሽኩቻ ፓርቲው ክፉኛ ታምሶ ነበር። ይህ መታመሰ ዴሞክራሲያዊ መፍተሄ ማግኘት ሥላልቻለ ጉዳዩን ወደፍርድ በማድረስ ዶ/ር ታዴዎስ በወንጀለኝነት ዘብጥያ እንዲወርዱ አድርጓል። ፓርቲው ሁለት ቦታ እነዲከፈልም ምክንያት ሆኗል። አሁን የእነ ማሙሸት አማረ የተባለው አንጃ በዚህ ወቅት ከፓርቲው የተቆረጠ ነው።

ታዲያ ይህ ሁኔታ ሠሞኑን መኢአድ ከአንደነት ጋር ውህደት ለመመስረት ሲነሳ የተለየ ገፅታ ይዞ ወጥቷል። ይህም የእነ አቶ ማሙሸት አማረ ቡድን ከፓርቲው መወጣቱ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ምልዐተ ጉባኤ መሙላት አለመቻሉ ያስከተለው ነው። ፓርቲው ችግሮችን በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርአት መፍታት አለመቻሉ ያስከተለወ የእነ አቶ ማሙሸት አማረ ቡድን ከፓርቲው ተቆርጦ መውጣት  የምልዐተ ጉባኤ መጓደል በማስከተል በፓርቲወ ሕገ ደንብ መሰረት የውህደት ውሳኔ የማሳለፍ አቅም አሳጥቶታል።

"ይህችም ከተማ ሆና ምን ወረሳት" እንዲሉ፣ በቅርቡ የተመሰረተው ሚጢጢው ሰማያዊ ፓርቲም በውስጡ በተቀሰቀሰ አለመግባባት እየታመሰ መሆኑን ሰምተናል። ሰማያዊ ፓርቲ ከተመሰረተ በኋላ በፓርቲው ሕገደንብ መሰረት በየአመቱ ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ ሲገባው አንዴም አለማካሄዱ በሥራአስፈፃሚውና በጉዳዩ ላይ ቅሬታ ባቀረቡ የምክር ቤቱ አባላት መሃከል በተነሳ ውዝግብ ትንሿ የሰማያዊ ፓርቲ ቤት አየተናጠች ነው።

የፓርቲው መስራችና ሊቀመንበር አቶ ይልቃል ጌትነት ፓርቲው ከተመሰረተ በኋላ ባሉት ያለፉ ሁለት አመታት ጠቅላላ ጉባኤ ፊት ቀርበው አለመገምገማቸውና ጭራሽ ጠቅላላ ጉባኤ አለመጥራታቸው ነው የተወሰኑ የምክር ቤቱ አባላት ዘንድ ቅሬታ የፈጠረው። ታዲያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደተናገሩት ይህ ቅሬታ  እነደታላቁ አንድነት ሁሉ አመራሮቹን በጡጫና በርግጫ አደባድቧል።

ይህ የ'አለን' ባዮቹ ሦስት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ማንነትና ምንነት ከተቃዋሚ ፓርቲዎች አማራጭ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች በሚጠብቀውና ብሄራዊ መብቶቹና ነፃነቶቹ አንድም ሳይሸራረፉ እንዲከበሩለት በሚፈልገው የኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት አሳጥቷቸዋል። የእነዚህ ፓርቲዎቸ ደጋፊዎች ጥቂት በአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ የሚገኙ በሕገመንግስታዊ ሥርአቱና በገዢው ፓርቲ ላይ ጭፍን ጥላቻ ያላቸው ዜጎች ብቻ ናቸው። እነዚህ ደግሞ የተቃውሞ ሰልፍ ከማድመቅና በማህበራዊ ሚዲያ ዘለፋ ከመቸክቸክ ያለፈ ለሥልጣን የሚያበቃ ድምፅ ማስገኘት የሚችሉ አይደሉም።

እንግዲህ እነዚህ ፓርቲዎች የተቋቋሙበት መሰረት የኢትዮጵያን ብሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብትና ነፃነት ማስከበር፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅማቸውን ማረጋገጥ ሳይሆን

በገዢው ፓርቲ፣ በሕገመንግስቱና በሕገመንግስታዊ ሥርአቱ ላይ ባላቸው ጥላቻና ጭፍን ተቃወሞ መሆኑ፣ እንዲሁም በውስጠ ዴሞክራሲ ድርቅ መታመሳቸው በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ቢያሳጣቸውም ይህን ችግራቸውን ማስተካከል ግን አልቻሉም ወይም አልፈቀዱም።

ከዚህ ይልቅ ቀልብ ሳቢ ሆነው ያገኙዋቸውን ጉዳዮች ያለወጉ በማራገብ ሕዝብን በመንግስት ላይ የማስነሳት አካሄድን የሙጥኝ ብለዋል። በዓለም ላይ አደገኛነቱ እየጎላ የመጣውን እስላማዊ አክራሪነት እስከመደገፍ የወሰዳቸው ይህ ሁኔታ ነው። ሕገመንግስታዊ ሥርአቱን በኃይል መናዳቸውን እንጂ ከዚያ በኋላ ሊፈጠር የሚችል አደጋን እንኳን ማየት እስኪያቅታቸው በጥላቻ ታውረዋል።

በአጠቃላይ የአንድነት፣ የመኢአድና ሰማያዊ ፓርቲዎች ለመመስረት ያበቃቸው ምክንያትና በውስጣቸው ያለው ሃገርን ለማስተዳደር የማይበቁ መሆናቸውን የሚያሳይ ቀውስ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ልበ አርቋቸዋል። ከህዝብ ልብ የራቀ ደግሞ ከህዝብ ድጋፍና ድምፅም ይርቃል።